ለጥቅም አዋልኳት በዶላር መንዝሬ(ተስፋሁን ሞላ) ፩

በላይ ቤት በታች ቤት አገኘኝ መከራ

ተቀጣጠለብኝ የሰዎች ቆራ

ያፈሰስኩት ደም አስነሳ አቦራ።
ሰርቻለሁ ጥሩ እኔስ ለሀገሬ
ለጥቅም አዋልኳት በዶላር መንዝሬ
ሸጥኳት ለፋሽስቶች በኢሮ መንዝሬ።
ጠብቄአለሁ እኔ የአባቶቼን አደራ
አሳልፌ ሰጠሁ ቅል ሳይቀር ቋንቁራ
ሸነሸንኩት ሁሉን ወንዝ እስከ ተራራ
አንድም አላስቀረሁ የሚሆን የጋራ።
መሬቱንም ሸጥኩት ህዝቡን አባርሬ
ደኑን አቃጥየ ጫካውን መንጥሬ
አብቅሉበት እሩዝ ሳይቀር ፍራ ፍሬ
ለቻይና ለህንድ ለአረቡ ቃፊሬ
አደልኳቸው ሁሉን በዶላር መንዝሬ
አንድም ሳላስቀር ለሃገሬ ገበሬ።
እነርሱ የተከሉት እንዲያፈራ ፍሬ
ነቃቅዬ ጣልኩት ከሥሩ ቆፍሬ
መልሶ እንዳይበቅል አፈሩን ሸርሽሬ።
እርሻውን የሚያርሰው አይገኝም በሬ
ነጣጥየዋለሁ በሬ እስከ ገበሬ
አስቀምጨዋለሁ አንገቱን ሰብሬ
ሲያማርር ይውላል እያለ አምለኬ ፈጣሬ።
አመጣለታለሁ ቃርሜ ማርሬ
ተዝናንቶ ይኖራል የሀገሬ ገበሬ
የሠራሁት ሥራ እኔ ለሀገሬ
በታሪክ ተጽፎ ይቀመጥልኛል በግል ማህደሬ።
እኮራለሁ እኔ በሠራሁት ስራ
ሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝብ በእኔ እየተመራ
ሳይረበው ሳይጠማው ሳያገኘው መከራ
ተዝናንቶ ይኖራል በእኔ እየተኩራራ።
መኖሪያ ቤት ቢያጣ በረንዳ እያስተኛሁ
ቢርበው ቢቸግረው
ስለ ቸሩ እግዚአብሔር እንዲል አሰኘሁ
ደልቶት እንዲኖር ሕዝቤን አደርጌአለሁ።
ለሥራ እንዳይወጣ መንገድ እየዘጋሁ
ለመዝናኛ ብዬ ጫትን አቀርባለሁ
ሕዝቡም እንዳያፍር አብሬ እቅማለሁ
በጫት ሲመረቃ ከሔድስ ጋራ ትግል አጋጥመዋለሁ
ሁሉም እንደ ቅጠል ሲረገፍ እኔ ብቻ እቀራለሁ።
የሕዝብን አደራ በብቃት ስዋጣው
ሰዎች ይጠሉኛል ከመሬት ተነስተው።

ለምን እንደሆነ አልገባኝ ነገሩ ፪
በውጭ ተቀምጠው ዶልተው ሲያወሩ
ካገር ቤት ይምጡና ገብተው ይሞክሩ
ለሚደርስባቸው ችግሩን ሳይፈሩ
ለሕዝቡ ይቁሙለት ገብተው ከአገሩ
በውጭ ሁነው ወሬውን አያውሩ።
 እኔስ ከሕዝቡ ጋር አብሬ እኖራለሁ
 እንርሱ ሲያለቅሱ እኔም እስቃለሁ
 እንዲሁም ሲበዛ እኔም አለቅሳለሁ
 የዉጩን ድንፋታ ቀረርቶ እየሰማሁ።
ሰውም አላገኘሁ ለእኔ የሚያዝንልኝ
እግዚአብሔር ብቻ ነው ለእኔ የቆመለኝ
በእርሱ የሚየአምኑትን አውጥቼ ስለ አባረርኩኝ።
 ይህን ሁሉ ሳደርግ እኔ ብቻየን ነኝ
 አንድም አላገኘሁ የሚተባበረኝ
 ግን ይሄን ሁሉ ስሠራ አንድም አልተሰማኝ
 ብቻዬን ነኝ ብዬ በእግዜር አላጉረመረምኩኝ
 እርሱ በሰማይ ደጅ ዋጋዬን ይከፈለኝ።
 ይቀጥላል፤

EthioLion.Com